
# ባሃኡላህ

## የአምላክ ክብር




**ባሃኡላህ የኢራን ዋና ከተማ በሆነችው በቴህራን ኖቬበር 12 ቀን 1817 ተወለደ። ከልጅነቱ ጀምሮ፣ የታላቅነት ምልክቶችን ይታይበት ነበር። በቤት ውስጥ የተወሰነ ትምህርት አግኝቷል ነገር ግን ትምህርት ቤት መግባት አላስፈለገውም፣ ምክንያቱም በተፈጥሮ እውቀት አምላክ ለግሶታል።**



አንድ ቀን ምሽት አባቱ፣ ባሃኡላህ በውቅያኖስ ውስጥ ሲዋኝ ህልም አዩ:: ከአካሉ የሚወጣው ብርሃን ውሃውን አበር ቶታል:: ረጅም ጥቁር ጸጉሩ በየአቅጣጫው ተንሳራፍቷል፣ ብዙ ዓሣዎችም ተከተሉት፣ እያንዳንዳቸው የአንድን ፀጉር ጫፍ ይዘዋል:: በነፃነት እና ያለ ምንም እንቅፋት ይንቀሳቀስ ነበር:: ይህ ህልም ባሃኡላህ ታላቅ እጣ ፈንታ እንደሚ ጠብቀው ከሚያሳዩ ብዙ ማስረጃዎች አንዱ ነበር::



ባሃኡላህ ወጣት ሳለ፣ በንጉሡ ቤተ መንግሥት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ተሰጠው፣ እሱ ግን እምቢ አለ፡፡ የተጨቆኑትን፣ የታመሙትን፣ ድሆችን ለመርዳትና ለፍትህ ዘብ በመቆም ጊዜውን ለማሳለፍ ፈለገ፡፡



ባሃኡላህ 27 ዓመት ሲሆነው፣ መምጣቱ ለዘመናት ሁሉ የተስፋ ቃል የተገባለትን የአምላክ መልዕክተኛ እንዲቀበሉ ሰዎችን ሲያዘጋጅ ከነበረው ከባብ የተጠቀለለ ጽሐፍ ተቀበለ፡፡ መልዕክቱን ከተቀበለ በኋላም ከጽኑ ተከታዮቹ አንዱ ሆነ፡፡



ባለሥልጣናቱ ባብ ያወጀውን እውነት ለመቀበል ፈቃደኛ ሳላልሆኑ በእርሱ የሚያምኑትን ለማሰቃየት ተነሱ፣ የባሃኡላህ መከራም ጀመረ። እ.ኤ.አ. በ1852፣ ተይዞ በሰንሰለት ታስሮ እጅግ አስፈሪ በሆነው የቴህራን እስር ቤት ውስጥ ተጣለ።



በዚህ እስር ቤት ውስጥ፣ በባብ እና ባለፉት ነቢያት ሁሉ ቃል የተገባለት እርሱ መሆኑን አምላክ ለባሃኡላህ ገለጸለት። ከዚህ ጨለማ እስር ቤት የእውነት ፀሀይ ወጥታ ዓለምን እያበራች በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ አዲስ ቀንን ወለደች።



ከአራት ወራት እስራት በኂላ መንግስት ባሃኡላህን ከትውልድ አገሩ አባረረው። በክረምቱ ከባድ ቅዝቃዜ፣ ባሃኡላህ እና ቤተሰቡ ከቴህራን ወደ ባግዳድ ረጅም ጉዞ አደረጉ።



በባግዳድ የባሃኡላህ ጥበብ እና ዝና በሁሉም አቅጣጫ ተስፋፋ። የእርሱን እርዳታ እና ምክር በሚፈልጉ ሁሉም ዓይነት ሰዎች ቤቱ ተጨናነቀ። የባሃኡላህን ተጽእኖ የፈራው መንግስት እሱን ከትውልድ አገሩ የበለጠ ለማራቅ ወሰነ።



# የሪዝቫን አትክልት ሥፍራ
## ኤፕሪል 1863

ባግዳድን ከመልቀቁ በፊት ባሃኡላህ ከከተማው ውጭ ባለ የአትክልት ስፍራ ውስጥ አስራ ሁለት ቀናት አሳልፏል፣ እርሱን ለመሰናበት ብዙ ጎብኚዎች ይመጡ ነበር፡፡ በዚህ የአትክልት ስፍራ፣ ባሃኡላህ ለዚህ ቀን የአምላክ መልዕክተኛ መሆኑን አውጀ፡፡ ለመጪዎቹ ዘመናት፣ ይህ የኤፕሪል ወር የአስራ ሁለት ቀናት ጊዜ የሪዝቫን በዓል ተብሎ ይከበራል፡፡ ባሃኡላህ ዓለም አቀፍ ተልእኮውን ያወጀበት ቀን ክብረ በዓል፡፡


ሱልታን አብዱ አል-አዚዝ
የኦቶማን ኢምፓየር


ኒኮላቪች አሌክሳንደር II ፣ የሩሲያ
ንጉስ



ፍራንዝ-ጆሴፍ,
የኦስትሪያ ንጉሠ
ነገሥት


ናፖሊዮን III, የፈረንሳይ
ንጉሠ ነገሥት


የፋርስ ናስረዲን
ሻህ


ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፒዮስ ዘጠነኛ


የእንግሊዝ ንግስት
ቪክቶሪያ


ዊልያም I,

የፕሩሲያ ንጉስ

**የባሃኡላህ ቀጣይ የግዞት ቦታ ቁስጥንጥንያ ከዛ ደግሞ አድሪያኖፕል ሲሆን ሁለቱም ዛሬ የቱርክ ከተሞች ናቸው:: እስረኛ እና ግዞተኛ የሆነው ባሃኦላህ፣ ከአድሪያኖፕል ለዓለም ነገሥታትና ገዥዎች መልዕክት ላከ:: ፍትህን እንዲያስከብሩ እና ስልጣናቸውን ተጠቅመው መከራን እና ጦርነትን እንዲያቆሙ መከራቸው::**



በአድሪያኖፐልም ልክ እንደበፊቱ የባሃኡላህ ዝና በክልሉ ነዋሪዎች መካከል ተስፋፋ፣ መንግሥትም እሱን ወደ ‘አካ የእስር ከተማ አርቆ ሊያባርረው ወሰነ። ይህ የእስር ከተማ ወንጀለኞች እና የአገሪቷ ነገር ቆስቋሾች ዳግመኛ ድምጻቸው እንዳይሰማ የሚላኩበት ነበር።



የእስር ሁኔታው በጣም ከባድ ነበር። አንዳንድ የባሃኡላህ ተከታዮች ወደ ‘አካ ብዙ ርቀት ተጉዘዋል፣ ነገር ግን ወደ እርሱ እንዲገቡ አልተፈቀደላቸውም። ሊያዩት የቻሉትም፣ ከሩቅ ሆነው፣ ከእስር ቤቱ መስኮት ወደ እነርሱ ሲያውለበልብ ብቻ ነበር።



በክልሉ ውስጥ ቁጥራቸው እየጨመረ የመጣ ሰዎች የባሃኡላህን ኃይል እና ግርማ ሲገነዘቡ ሁኔታዎች ቀስ በቀስ ተሻሻሉ። በመጨረሻዎቹ የህይወት ዘመኑ ከከተማው ቅጥር ውጭ በሚገኘው ባህጂ በሚባለው ትልቅ ቤት ውስጥ ኖረ። በአካ፣ ባሃኡላህ ኪታብ-ኢ-አቅዳስ የተባለውን እጅግ ቅዱስ መፅሐፉን ጨምሮ ለሰው ልጅ ብዙ መመሪያዎችን ገልጿል።



ሜይ 1892 ባሃኡላህ አረፈ። በአሁኑ ጊዜ በሚያማምሩ የአትክልት ስፍራዎች የተከበበው ባህጂ ውስጥ ያለው መካነ-መቃብሩ በምድር ላይ ካሉት ሁሉ የተቀደሰ ቦታ ነው። በየዓመቱ፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ከዓለም ዙሪያ የሚመጡ ሰዎች አክብሮታቸውን ለመግለጽ እና ጸጥ ባለ አከባቢ ውስጥ ለመጸለይ እና ለማሰላሰል የመካነ-መቃብሩን ቦታ ይጎበኛሉ።

Copyright © 2007, 2023 by the Ruhi Foundation, Colombia
All rights reserved. Edition 2.1.1.PE. May 2023, published in Amharic

Ruhi Institute
Email: instituto@ruhi.org
Website: www.ruhi.org